# <u>የኢትዮጵያ ሕዝብ የጋራ ትግል ሸንጎ (ሸንጎ) ተመሠረተ</u>





**የኢትዮጵያ ሕዝብ የጋራ ትግል ሸንጎ መመሥረትን አስመልክቶ ከግንቦት 10 ቀን እስከ ግንቦት 13 ቀን 2004 ዓ.ም (May 18-21, 2012) ድረስ በካናዳ ዋና ከተማ በኦታዋ አልጎንኩይን ኮሌጅ መሰብሰቢያ አዳራሽ የተደረገው ጉባዔ መግለጫ፦**

የኢትዮጵያ ሕዝብ ለዘመናት በመሣሪያ ኃይል እራሳቸውን በመንግሥትነት የሰየሙትን ጨቋኝ ገዥዎች በሕዝባዊ ትግል ቢጥልም የፈለገውን በራሱ ፈቃድ መርጦና ሸሮ የሚያስተዳድሩትን መሪዎች የመቆጣጠሩ ሕዝባዊ ሥልጣን ባለቤት ለመሆን አልቻለም። አንዱ ገዥ ሲወድቅ ሌላው ጨቋኝ እየተተካ የሕዝቡ ኑሮ ውድቀት ጨመረ፣ ሰብዓዊ መብት ጥሰቶች ሳይገታ የኢትዮጵያን ሉዓላዊነትና የግዛት አንድነት የሚሸረሽር መሬቱን ሳይቀር ለባዕድ ባለሀብቶች የሚሸጥ እኩይ መንግሥት በሥልጣን ላይ ይገኛል።

በአሁኑ ወቅት በሥልጣን ላይ የሚገኘውን የህወሓት/ኢህአዴግ መንግሥት ለመታገልና የኢትዮጵያን ሕዝብ የሥልጣን ባለቤት ለማድረግና ከጭቆና ለመላቀቅ ከዚህ በፊት እንዳደረገው ሁሉ ዛሬም ገንፈሎ ገዥዎቹን ለመጣል የሚነሳበት ወቅት መሆኑን በርካታ አመልካች ሁኔታዎች አሉ። ይህን የሕዝብ እምቢተኝነትና ሕዝባዊ አመጽ ብሎም የለውጥ መነሳሳት እንደተለመደው ሌላ የማይፈለግ ኃይል በድጋሚ እንዳይነጥቀው የሕዝቡን ትግል በሥርዓት አደራጅቶ ለውጤት ማብቃት የሁሉን ሕዝብ የጋራ ተሳትፎና ትብብር የሚጠይቅ በመሆኑ በተናጠል የሚደረጉ ትግሎች እስከ ዛሬ ለውጤት ካለመብቃታቸውም በላይ አንዱን ጨቋኝ ቀይሮ በሌላ መተካት እንዳይሆን የተባበረና አስተማማኝ ትግል ለማድረግ በኅብረት መታገል አማራጭ የሌለው ሆኖ ተገኝቷል።

በዚሁም መሠረት በአንድነትና በጋራ ለመታገል ኢትዮጵያን እንደ ሀገር የመቀበሉና በሀገሪቱ ውስጥ የሰፈነው አረመኔ አገዛዝ እንዲወገድ የሚፈልጉ የተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶች በተለያዩ ደረጃ የተቋቋሙ የማኅበረሰብ (civic) ማኅበራትና ግለሰቦች ለማሰተባበር ለሁለት ዓመት ገደማ በሁሉን አቀፍ ጉባዔ ለአንድነት ኅብረት ምሥረታ ሁሉንም የፖለቲካ ድርጅቶች የሲቪክ ማኅበራትና ግለሰቦች በአካል፤ በኢሜይል በተለያዩ በራሪ ጽሁፎችና መግለጫዎች የእንሰባሰብ ጥሪ እስከ ጉባዔው መጀመርያ ድረስ ያለማቋረጥ አቅርቧል።

ይህንኑ ጥሪ ተቀብለው የተገኙ፣

## ሀ. የፖለቲካ ድረጅቶች

1. የኢትዮጵያ ዴሞክራሲዊ ኃይሎቾ ሕብረት
2. የኢትዮጵያ ህዝባዊ አብዮታዊ ፓርት ዲሞክራት
3. ትግራይ ዴሞክራሲያዊ ትብብር

4. ትንሳኤ ኢትዮጵያ የአርበኞች ህብረት

5. ታጠቅ አርበኞች ግንባር

6. የኢትዮጵያ መድህን ዲሞክራሲያዊ ፓርቲ (መድህን)

## ለ. የሲቪክ ማኅበራት

1. የኢትዮጵያ ፖለቲካ እስረኞች አንድነት ኮሚቴ በካናዳ (SOCEPP-CA)
2. የኢትዮጵያ የሲቪክ ማህበራት ስብስብ በእንግሊዝ ሀገር
3. የኢትዮጵያ ህዝባዊ መድረክ በሲያትል (በታዛቢነት)
4. ኢትዮ-ካናዳ የዲምክራሲ መድረክ
5. የኢትዮጵያ ብሄራዊ ሽግግር ኮንስል (ENTC)
6. የኢትዮጵያውያን ጋራ መድረክ በኖርወይ
7. የዳላስ ሁሉን አቀፍ ጉባኤ ድጋፍ ኮሚቴ

እንዲሁም በርካታ አገር ወዳድ ግለሰቦች በተገኙበት ግንቦት 10 ቀን 2004 ዓ.ም በኦታዋ ከተማ የአራት ቀናት ጉባዔ ጀመሩ። ጉባዔው የተጀመረው በሃይማኖት መሪዎች ፀሎት፣ ዱዓና ቡራኬ ሲሆን በመቀጠልም ለጉባዔው መሳካት በልዩ ልዩ ችግሮች ምክንያት በአካል መገኘት ያልቻሉ የፖለቲካ ድርጅቶች የሲቪክ ማኅበራትና ታዋቂ ግለሰቦች የመልካም ምኞትና የድጋፍ መግለጫ መልዕክቶችን አስተላልፈዋል።

ጉባዔው ስብሰባውን የሚመሩ ጊዜያዊ አመራሮች ሊቀመንበር፣ ም/ሊቀመንበርና ሁለት ፀሐፊዎች እንዲሁም የውሳኔ አርቃቂና ቃል አቀባዮችን በመሰየም ሥራውን ቀጠለ። በሁለት ቀናት ውሎው የኢትዮጵያን ወቅታዊ ሁኔታ በተመለከተ የቀረበለትን ጥናታዊ ጽሁፍ መነሻ በማድረግ የሀገሪቱን ነባራዊ ችግሮች መፍትሄ ሊሆኑ የሚችሉ ሃሳቦች ላይ በሰፊው መክሯል። ከዚህም በተጨማሪ የኅብረት አስፈላጊነት፣ የቀድሞ ኅብረቶችና ተመክሮዎች በነዚህ ታሪካዊ ሂደቶች ላይ በመነሳት ምን ዓይነት ኅብረትና ስትራቴጂ መንደፍ ይቻላል የሚሉ ጥልቅ ጥናታዊ ፅሁፎች ቀርበዋል። ውይይትም ተካሂዶባቸዋል። በዚሁም መሠረት የትግሉ ራዕይ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ የኢትዮጵያን ሕዝብ ሙሉ ነፃነትና የሥልጣን ባለቤትነት ለማረጋገጥ የሚደረግ ትግል መሆኑን አምኖ ተቀብሏል። ይህንኑ ገቢራዊ ለማድረግና የህወሓት/ኢህአዴግን መንግሥት ማስወገድ አስፈላጊ መሆኑን አምኖ አጽድቋል። ጉባዔው የትግሉ አጋር የሚሆኑትን ኃይሎች ማንነት በተመለከተም የትግል ጥሪ ማሰባሰቢያ ሆነው በሁሉን-አቀፍ ጉባዔ አዘጋጅ በኩል የቀረቡት አምስት መሠረታዊ የማሰባሰቢያ መርሆዎች የኢትዮጵያ ሕዝብ የጋራ ትግል ሸንጎ ለመቀላቀልና

አብሮ ለመታገል ለሚፈልጉ ወገኖች ሁሉ የሚከተሉት የማታገያና የማሰባሰቢያ መርሆዎች እንዲቀበሉ ጥሪ አቅርቧል፤

1. በኢትዮጵያ ሕዝብ የሥልጣን ባለቤትነትና ሉዓላዊነት እንዲሁም በሀገሪቱ የግዛት አንድነት ላይ ግልጽና የማያወላውል ዕምነት መኖር፤
2. የማንኛውንም ኢትዮጵያዊ ግለሰብ ዴሞክራሲያዊና ሰብዓዊ መብቶቹን ማክበር፤ በየድርጅቶች ውስጥና በምንሰባሰብበት የኅብረት ማዕቀፍ ውስጥ ዴሞክራሲያዊ ግንኙነቶችንና አሠራሮችን ለማስፈን መሥራት፤
3. በኢትዮጵያ ውስጥ የሕግ የበላይነት እንዲኖር ጸንቶ መታገል፤
4. በኢትዮጵያ ሕዝብ መካከል ምንም ዓይነት አድላዊነት እንዳይኖርና ሁሉም በሕግ ፊት እኩል ዜጎች መሆናቸውን ማመንና በተግባርም ማስረገጥ፤
5. የህወሓት/ኢህአዴግ መንግሥትና ሥርዓት የአፈናና የጭቆና ሥርዓትና በመሆኑ መለወጥና በዴሞክራሲያዊ አስተዳደር መተካት እንዳለበት ማመን፤

ጉባዔው በዚሁ የአራት ቀናት ቆይታው የኅብረት ድርጅት መመሥረት አስፈላጊነት በማመን ኅብረቱ እንዲመሠረት በሙሉ ድምፅ ወስኗል።ጉባዔው ይህን ከወሰነ በኋላ የኅብረቱ መጠሪያ ስያሜ በድምፅ ብልጫ "የኢትዮጵያ ሕዝብ የጋራ ትግል ሸንጎ (ሸንጎ)" ከዛሬ ጀምሮ "ሸንጎ" እየተባለ በአጭሩ እንዲጠራ ውሳኔ አስተላልፏል።

ሸንጎው የድርጅቱን ደንብ ሲያፀድቅ አርማውን በተመለከተ ደግሞ የኅብረቱን መርሆዎች የሚያንፀባርቅና የትግሉን ራዕይ አመልካች እንዲሆን የመንደርደሪያ ሃሳቦችን ሰጥቶ ዝርዝር ሥራው በባለሞያ ተሠርቶ እንዲቀርብ መመሪያ ሰጥቷል።

ጉባዔው የድርጅቱን መዋቅር በተመለከተም የኅብረቱ ሸንጎ፣ ምክር ቤትና ሥራ አስፈፃሚና ልዩ ልዩ የተግባር ዘርፎች እንዲኖሩት ስምምነት ላይ ደርሷል። በዚሁ መዋቅራዊ አሠራር መሠረት የድርጅቱን ምክር ቤት የሰየመ ሲሆን ምክር ቤቱ በበኩሉ ድርጅቱን እስከ ቀጣዩ ጉባዔ ድረስ እንዲመሩ፤

1. ዶ/ር ኤርምያስ ዓለሙ - ሊቀመንብር
2. ፕ/ሮ አቻምየለህ ደበላ - ም/ሊቀመንበር
3. አቶ ግደይ ዘራጽዮን - ፀሐፊ
4. አቶ አስርደው ከበደ - የፋይናንስ ሃላፊ ሆነው እንዲሠሩ ሲመርጥ ይህንኑ

ጉባዔተኛው ያፀደቀው ሲሆን ቀሪ የሥራ ድልድሉን ምክር ቤቱ እንዲያሟላ አመራር ሰጥቷል።

ሸንጎው ያወጣቸውንና ያፀደቃቸውን አምስት መርሆዎች የሚቀበሉ የፖለቲካ፣ የሲቪክ ድርጅቶችና ግለሰቦች የኅብረቱ አባላት እንዲሆኑ በሙሉ ድምፅ ወስኗል። እንዲሁም በአሁኑ ወቅት የኅብረቱ አባል ያልሆኑ የፖለቲካ ድርጅቶች የሲቪክ ማኅበራትና ግለሰቦች የኅብረቱን ትግል እንዲቀላቀሉ ጥሪ አቅርቧል።

ሸንጎው በከፍተኛ ደረጃ ከተነጋገረባቸው ጉዳዮች አንዱ ካለፉት የኅብረት ምሥረታ ሂደቶች ተመክሮ በመነሳት በኅብረቱ አባላት መካከል በሚነሱ ልዩነቶችን አያያዝና አፈታት ከመረመረ በኋላ ሙሉ ሥልጣን ያለው የሽማግሌዎች ምክር ቤት እንዲቋቋም ወስኖ ሽማግሌዎቹንም መርጧል።

ሸንጎው ለምክር ቤቱ ከሰጠው መመሪያ አንዱ የኢትዮጵያ ብሄራዊ የሽግግር ምክር ቤትን ለመመሥረት በመጪው ጁላይ 1-3, 2012 በሚደረገው ጉባዔ ላይ የሸንጎው ተወካዮች እንዲገኙና የሁለቱ ግንኙነት ተጠናክሮ እንዲቀጥል መመሪያ ሰጥቷል፡፡

ግንቦት 13 ቀን 2004 ዓ. ም

May 21, 2004